በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
The government nation state of Tigray
የመቐለ ከተማ አስተዳደር
City administration Of Mekelle
Tel. 41 01 92/41 01 93 Fax 41 01 99/ 41 69 63

መጋቢት 19፡ 2001 ዓ.ም

March 26, 2009

# የምሥጋና መልእክት

ክቡራትና ክቡራን

በመጋቢት 12፡2001 (March 21, 2009) በቱዩቢንገን ከተማ ጀርመን የመቐለ እና የቱዩቢንገን የእህትማማቾች ከተሞች ጉዳይ በሚመለከት በተቆርቋሪ ኢትዮጵያውያን ስለተደረገው ሰለማዊ የድጋፍ ሰልፍ ዜና ደርሶኝ በጣም እንደተደሰትኩኝ በመግለፅ ጊዚያችሁና ገንዘባቹህ በመለገስ በቦታው ተገኝታቹህ ድጋፋችሁን ለገለፃቹሁልን ወገኖች ልባዊ ምስጋናየን ይድረሳቹህ እላለሁ፡፡ ከአሁን በፊት ጥቂት ግለሰቦች በቱዩቢንገን ከተማ የታሰበው የሁለት ከተሞች የእህትማማችነት መንፈስ በመፃረር አቋም ወስደው በከተማው ነዋሪ አሳፋሪ ትዝብት እንዳተረፉ ይታወሳል፡፡ መቐለ ከተማ የቱዩቢንገን ከተማ እህት ከተማ እንድትሆን የታጨችው ከተማችንና የከተማውን ህብረተሰብ በደንብ በሚያውቁ የቱዩቢንገን ነዋሪ ባደረጉት አነሳሽነት ሆኖ ይህ ሓቅ ብቻ ለከተማው ነዋሪ በጣም አኩሪ ነው፡፡ የእህት ከተማው ሀሳብ ለሁለቱም ከተሞች ጠቃሚነት እንዳለው እያስታወስኩኝ የሃሳቡ ምንጭ ቱዩቢንገን ባላት ከተለያዩ ከተሞች የመቀራረብ ፖሊሲ መሆኑ እንዲታወቅ ያስፈልጋል፡፡

ኢትዮጵያ የነበርዋት የተለያዩ መንግሥታት አንዳንድ የአገሪትዋን ክፍሎችና ነዋሪዎችን እንደጠላት በመፈረጅ ይህ የማይባል ጉዳት ሲያደርሱ ነበር፡፡ ሲያስፈልጋቸው በአውሮፕላን ቦንብ በመደብደብ ሲያሰኛቸው እግረኛ ሃይልን በመላክ ሰለማዊውን ህዝብ በመጨፍጨፍ ትልቅ ወንጀል እንደፈፀሙ ስናስታውስ የመቐለ ነዋሪም የዚህ ግፍ ተቋዳሽ እንደነበር ይታወሳል ይህ ሁሉ ግፍ እንዳይፈፀም በህዝባዊ ጠንካራ ክንድ ታግደው ዳግመኛ ዕድል እንደማይኖራቸው በመረዳት አሁን ሥራየ ብለው የያዙት በሠው አገር ሆኖ አሣፋሪ ሥራ መሥራት ነው፡፡

ሶስት ከተሞች (መቐለ፣ ሞሺ ከታንዛንያ እና በዌ ከካሜሮን) ለመጨረሻው ግምገማ ታጭተው እንደነበር ሳስታውስ ተመራጭ ከተማ ማን ይሁን ማን አንድ የአፍሪካ ወንድም ህዝብ ስለሚሆን ደስታው የሁላችን መሆን አለበት፡፡

የቱዩቢንገን "የእህት ከተሞች አጣሪ ኮሚሽን" የሚያደርገው ውሣኔ ሁላችን በፀጋና በኩራት የምንቀበለው መሆን አለበት፡፡

"ከሠላምታ ጋር"

Fescha Zeryhun Weldu
Mayor of Mekelle City